# ***ጥምረት ለነጻነት ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ***

ግንቦት 11 ፣ 2003

**ከ*ጥምረት ለነጻነት ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ* የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ**

## ***በህዝባዊ አንድነትና በጋራ አላማ የሚመራ የእምቢተኛነት ቁጣ ካለመበት ይደርሳል።***

አይቀሬው የህዝቡ እምቢተኛነት ቁጣ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሰማይ ላይ እያስገመገመ ነው። የህዝቡ ቁጣ ትኩረት ሊያደርግባቸውና የጋራ መታገያ ነጥቦች አድርጎ ሊያነሳቸው የሚገቡ ጉዳዮች የፖለቲካ ድርጅቶችና በሲቪክ መሃበራት የወጣቶች ንቅናቄና የመላው ማህበረሰብ መነጋገሪያ ርእስ ሆነዋል። በሁሉም አካላት በኩል ያለው ስሜት ህዘብ በጋር የሚያተኩርባቸውና በሁሉም ዜጋና ማህበረሰብ ድጋፍ ሊያገኙ የሚችሉ መታገያ ነጥቦች ላይ የጋራ አቋም መያዝ ለትግሉ መቀላጠፍ ታላቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ነው። **የ*ጥምረት ለነጻነት ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ*** የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችን የሲቪክ ማህበራትንና የወጣቶች ንቅናቄዎችን ካማከረና የሚያነሷቸንም ጥያቄዎች ከመረመረ በኋላ ከዚህ በታች የተቀመጡት ጥያቄዎች በእምቢተኛነት የሚነሳውን ህዝብ የሚያስተባብሩና ለምላሻቸው በጋራ ተግቶ እንዲንቀሳቀስ የሚያስችሉ ናቸው የሚል ጽኑ እምነት አለው። **የ*ጥምረት ለነጻነት ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ*** እነዚህ ጥያቄዎች በማንሳት ከመለስ ዜናዊ አገዛዝ ጋር ለመፋለም ከሚዘጋጀው ህዝብ ጎን ይቆማል። ከተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራትና የወጣት ንቅናቄዎች ጋር ለነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ማግኘት በጋራ ይታገላል።

1. *በሃገሪቱ እስር ቤቶች የሚማቅቁ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አሁኑኑ ይፈቱ። የሰው ልጆች ማረጃ ቄራና የሰቆቃ ስራ መፈጸሚያ የሆነው የማእከላዊ እስር ቤት ባስቸኳይ ፈረሶ ለዘላለሙ ይዘጋ።*
2. *በኦፊሴል ያልታወጀው ግን በተግባር በስራ ላይ የዋለው የኣስቸኳይ ጊዜ ኣዋጅ ይነሳ። በሃገሪቱ ህገ መንግስት የተደነገጉት የመናገር: የመጻፍ: የመሰብሰብ: ሰላማዊ ስልፍ የማድረግ መብቶች ሙሉ በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አሁኑኑ እንዲከበሩ። እነዚህ መሰረታዊ የሰብአዊና የሲቪል መብቶችን ለመጣስ የተደነገጉ ህጎች በሙሉ፤ ባለፉት ጥቂት አመታት የወጡትን የጸረ ሽብር ህግ፤ የፕሬስ ህግና፤ የመያድ ህጎችን ጨምሮ እንዲሰረዙ።*
3. *ወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ የህዝብን ፍትሃዊና ህጋዊ መብቶችና ጥያቄዎች ለማፈን ባለፉት 20 አመታት በተለያዩ አካባቢዎች በተለይ ደግሞ በኦሮምያ፣ በኦጋዴንና በሌሎችም ክልሎች ህዝቦች ላይ የሚካሄደውን ወታደራዊ የእመቃ ዘመቻ አሁኑኑ ይቁም።*
4. *በቅርቡ በነዳጅ ላይ የተደረገውና የዜጎችን ህይወት ለከፋ የኢኮኖሚ ስቃይ የዳርገው በነዳጅ ዋጋ ላይ የተደረገ ጭማሪ እንዲነሳ፤*

   *የአገዛዙ የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማስተካካያ እስኪበጅለት ድረስ ይህ የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ችግር ላይ ለጣላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ዳቦ፣ ስኳርና እህልና ዘይት የመሳሰሉት የመሰረታዊ ፍጆታ እቃዎች ባስቸኳይ ከመነሻው የመንግስት ድጎማ ተደርጎላቸው ለህብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚደርስበት መንገድ ይመቻች። የወያኔ የማዳበሪያ አከፋፋይ ኩባንያዎች በሞ ኖፖል በያዙት ንግድ ገበሬውን መበዝበዛቸው ያብቃ። ከባንያዎቹ ያለአግባብ ባካሄዱት ዘረፋ ባልእዳ አድርገው የሚያሰቃዩት ገበሬ ከእዳው ነጻ ይሁን።*
5. *የኢትዮጵያን ህዝብ ለአለም አቀፍ ጌቶች ባሪያ የሚያደረገው መሬት ለባእዳን አሳልፎ የመሸጥ ፖሊሲ አሁኑኑ ይቁም። በዚህ ረገድ የተደረሱ አለም አቀፍ ውሎች በሙሉ አሁኑኑ ይሰረዙ።*

# ጥምረት ለነጻነት ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ

6. *የመለስ ዜናዊና የቤተሰቡ ንብረት ባስቸኳይ ይወረስ። መጠኑ በውል በማይታወቀው የመለስ ቤተሰብና የቅርብ ባለሟሎቹ የሙስና ተግባራት ላይ የምርመራ ስራ አሁኑኑ ይጀመር ።*
7. *መለስ ዜናዊ ባስቸኳይ ከጠቅላይ ሚስትርነቱን ይነሳ ። የመንግስትን ስልጣን ባስቸኳይ ይልቀቅ።*
8. *ህገ ወጥ በሆነና በተጭበረበረ ምርጫ የተቋቋሙት የህዝብ መወሰኛና የፌደራል ምክር ቤቶች አሁኑኑ ይፍረሱ። ዋናዎቹና ሁሉም የነጻነት ንቅናቄዎችና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሁም የሲቪክ ማህበረሰባት ተወካዮች የሚሳተፉበት፣ አላማው ማህበራዊ ፍትንህንና ዴሞክራሲን ማንገስ የሆነና በአጭር ጊዜ በነጻ የምርጫ ተቋምና ኣለምኣቀፍ ታዛቢዎች ሙሉ ለሙሉ በተመሰከረለት ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ዴሞክራሲያዊ መንግስት የሚያቋቁም የሽግግር መንግስት ይቋቋም።*

***ለጋራ ድል,! በጋራ አላማ! ለነጻነታችን በቃ ብለን በአንድነት እንነሳ!***

**Contact address: pr@timret.org**